# የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ

# *Ethiopian Civil Service University*

Quarterly magazine
January-March
2024

*Committed to Excellence in the Public Sector!*

## ኢሲሰዩ ባለ ስምንት ወለል አዲስ ህንጻ ለማስገንባት ውል ተፈራረመ



## የኢሲሰዩ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሰራተኞቹ የምስጋና ፕሮግራም አደረጉ



## ኢሲሰዩ ካውንስል የ2016 የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን ግምገማ አካሄደ



# ራዕይ

**ፐብሊክ ሴክተሩን ከመገንባት አኳያ በ2022 በዘርፉ ከተሰማሩት ተቋማት መካከል የላቀ ፣ በቴክኖሎጂ የዘመነና ተወዳዳሪ የአቅም መገንቢያ ተቋም መሆን**

# ተልዕኮ

**ፐብሊክ ሴክተሩ ውጤታማ የህዝብ አገልጋይ ሆኖ እንዲሰራ አቅሙን በስፔሻላይዝድ ትምህርት ፣ በስልጠና ፣ በማማከር ፣ በጥናትና ምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎቶች በቀጣይነት መገንባት**

# እሴቶች

**ተገልጋይ ተኮር**
**ልቆ መገኘት**
**ተባብሮ መሥራት**
**ሁሌም መማር**
**ፈጠራን ማበረታታት**
**ዘለቄታዊ ውጤታማነት**
**ብዝሀነትን መቀበል**
**ትኩረት ልዩ ድጋፍ ለሚሹ**

# Table of Contents

*TI organizes the 1st In-Campus Academic Dialogue* 1

*ECSU President discusses with Deputy Head of EUto the AU* 2

*HOCHSCHULE KEHL UNIVERSITY DELEGATES VISIT ECSU* 3

*ECSU and KSG Sign MoU* 3

*ECSU) officially handes Over the Assosa University Campus Master-plan and Landscape Design Project* 4

*ECSU Gives Training to the Academic Staff* 5

**ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆን ለዩኒቨርሲቲዎች ትልቅ ዕድል እንጂ ስጋት አለመሆኑ ተገለጸ፡** 6

**የኢሲሰዩ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሰራተኞቹ የምስጋና ፕሮግራም አደረጉ** 8

**ኢሲሰዩ ባለ ስምንት ወለል አዲስ ህንጻ ለማስገንባት ውል ተፈራረመ** 9

**ኢሲሰዩ ካውንስል የ2016 የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን ግምገማ አካሄደ** 11

**ከአቶ አለሙ ሲሳይ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ........13**

# TI organizes the 1st In-Campus Academic Dialogue

Ethiopian Civil Service University ( ECSU ) Training Institute (TI) organized the 1st In-Campus Academic Dialogue under the theme of " Defining Scholars and Their Duties in the Modern Era" on 15 February 2024 at Hidasse Hall.




On the opening of the dialogue, Dr. Azebe Assefa, Dean of Training Institute, welcomed the presenter and the participants and said that holding the academic dialogues and fostering the culture of dialogue at ECSU is one of the priorities of the strategic goals of the university. In this regard, ECSU Training Institute cascaded this goal and launched this scholarly dialogue program that brings together the academia and discusses various economic, social and political issues, Dr. Azeb said. She also noted that the primary objective of this dialogue is to foster academic culture at ECSU by bringing members of the academic community from various disciplines and creating a space of sharing diverse voices which can be heard and respected. The academic dialogue evokes deep insight and provides the overall framing of being a scholar or an academician Dr. Azeb noted. She also thanked the organizers of the dialogue and all the participants

The speaker of the educational dialogue, Dr. Samson Estifanos, presented detailed explanation of the defi-



nition, operational standards and basic personality characteristics of being a scholar. According to him, currently, people use the words scholar, elite, and intellectuals interchangeably to describe the academic society. He said that being a scholar is not only having knowledge in different fields of study; it should be integrated with being honest and foreseeing the future. Scholars should meet the basic operational standard that includes having specialized knowledge at least in one field of study, possessing an intellectual mind that can dig out evidence based knowledge, discharging the social responsibilities expected from him or her and possessing the basic personality and characteristics of intellectual, Dr. Samson explained.

He also expounded on ten basic characteristics that define intellectuals. According to him, these ten characteristics are a scholar/ or an intellectual person possesses continuous knowledge and wisdom, has an inquisitive mind, preserves and disseminates evidence based knowledge, understands and takes care that he influences the society, always stands by the side of truth, prepared himself for sacrifice, sees all people equally, serves as an ambassador of peace between the government and the community, does not say that he knows everything, and does not withdraw himself from the political arena. Finally, Dr. Samson underlined that scholars need to take care of their actions and speeches being aware of the influence that exerts on the society and work hard for the next generation and discharge their responsibilities in a professional manner.

Dr. Samson Estifanos is Doctor of Medicine and Doctor of Theology with huge educational and work experiences and currently working freelancer as a medical and social researcher in Ethiopia.

# ECSU President discusses with Deputy Head of EUto the AU

Professor Fikre Dessalegne, Ethiopian Civil Service President, discussed with H.E. Riccardo Mosca, Deputy Head of Delegation European Union to the African Union on further strengthening the bilateral relations of ECSU and Kehl University in Germany on January19, 2024 at Hidasse Hall.

The President welcomed H.E. Riccardo Mosca, Deputy Head



of EU Delegation to African Union and University Schol-



ars and students from Kehl University, Germany. He added: 'I am pleasured to see scholars from different background and different countries which is a valuable input for working together in the areas of public services. ' The president said that as a higher Institution, one of ECSU strategic plan is partnership, internationalization and networking, so we have interest to further strengthening the tie with Kehl University. As we see, the progress of masters' program in public Management in International relations which we started in collaboration with kehl University is one of the successes that has brought by collaborative effort he added. He also explained the overall strategic plan of ECSU on the Internationalization and partnership and the interest of working together in different areas with Kehl University. Dr lemma Gudissa, ECSU Vice President for academic affairs, on his part, welcomed the Delegates and explained the strengthening of collaboration between the two institutions in different aspects in the future .He also noted that to further strength the masters' program and open PhD program in collaboration with Kehl university .Besides, he briefly explained the University's vision, mission, and values to the representatives and his discussion with kehl university Rector on the bilateral issues . Dr. Joachim Beck, Rector of Kehl University, explained that how the international cooperation creates a learning environment and understand different system of government and practices in each country and opportunities to understand the different cultures in different countries. He also explained that in the collaborative masters' program five universities from four countries are working together and ECSU is one of the partner institute. He also briefed that the two institutions have the same vision which are working on Public service capacity building. So it possible to work together in administrative culture and developed the two years masters' program to PhD project he underlined. Onur Yel, Counselor of culture and Press representing Germen Embassy in Ethiopia thanked the hospitality of the Ethiopian and Civil Service University. He also emphasized developing cooperation among different institutions is very important and wished the students for the successful accomplishment of the program. Finally, Students raised different questions for H.E. Riccardo Mosca and he respectively answered the questions raised by the students.



## HOCHSCHULE KEHL UNIVERSITY DELEGATES VISIT ECSU

Visiting lecturers from HOCHSCHULE KEHL University, Germany, paid an educational visit to Ethiopian Civil Service University for fifteen days (Janua13 -28, 2024).

The delegates were welcomed by Dr Lemma Gudissa, ECSU Vice president for Academic Affairs and discussed on the strengthening of their partnership and



collaboration between KEHL University and Ethiopian Civil Service University. He also explained ECSU success since its establishment and the importance of academic alliance from different institutions .ECSU is working with international and local institutions, so such event is one of its academic exercise he added. Ten professor from Kehl University and two from Ethiopian Civil Service University have been giving a face to face lecture for 17 students recurring from different Universities of South Africa, Zambia, Kenya, Germany and Ethiopia for 2 weeks .



The face to face course has been giving based on the tie between Ethiopian Civil Service University and HOCHSCHULE KEHL University to give masters' program in public Management in International relations.

The University of Public Administration in Kehl is one of the most renowned institutions of its kind in Germany. It was founded in 1971 and enlarged in the 1980s. Currently, the University employs 42 full-time professors and approximately 250 visiting lecturers. The sole purpose of Kehl University is to prepare its students for careers in public service.

## ECSU and KSG Sign MoU

Ethiopian Civil Service University Signed a Memorandum of Understanding (MoU) with Kenyan School of Governance to collaborate on building the capacity of public service.

The MoU was signed by the president of ECSU Professor Fikre Dessalegne and the Kenyan delegation representative during the 36th Ethiopia-Kenya Joint Ministerial Commission (JMC) held at Addis Ababa on 19th February 2024 . The 36th Ethiopia-Kenya Joint Ministerial Commission (JMC) is targeted to promote bilateral relations between Kenya and Ethiopia on different areas.



# ECSU) officially handes Over the Assosa University Campus Master-plan and Landscape Design Project

Ethiopian Civil Service University (ECSU) officially handed over the Assosa University Campus masterplan and landscape design project to Assosa University on January 15, 2024. Assosa University President Dr. Kemal Abdurahim has received the project design from Dr. Alemayehu Debebe, ECSU Vice President for Research and Partnership.

According to the project coordinator Ato Lisanework Sileshi, the project was conducted by ECSU Consultancy Service unit and the major purpose of the project was a preparation of physical plan for the Assosa University campus based on the University's ten years strategic plan. The project made an effort to incorporate the university's future expansions and constructions to meet further needs of the university in the future. The landscape design also take into account the climate condition of Asosa city in order to make the university campus suitable for the teaching learning processes.







He also noted that, apart from the income generated by the project, the preparation of this project opens an opportunity for ECSU to unveil its capability in designing other similar projects for different institution in need of such projects. In addition to building the image of the university, it was also a project where the university experts have gained practical knowledge and experience, Lisanework added. On the project, ten ECSU scholars were involved and it took a total of one year for completion. It is also known that ECSU has prepared and handed over different masterplan and landscape designing projects for different institutions and city administrations.

# ECSU Gives Training to the Academic Staff

Ethiopian Civil Service University, Academic Affairs Vice President office, in collaboration with the Federal Education and Training Authority gave a two days training on Education Quality Enhancement to the academic staffs from April 8-9, 2024 at Hidasse Hall.

In his welcoming speech, Dr. Lemma Gudissa, Vice President for Academic Affairs, welcomed the participants of the program and briefed the major objective and importance of the training program. According to him, although the problem in connection to the accessibility to formal education at the national level has been resolved, the issue of quality education is still a serious problem and remained the focus area of the education sector. In order to alleviate this problem, the Federal Government and Ministry of Education have been rigorously taking different actions and reform strategies. In connection to this, ECSU has given due attention to the quality of education and exerted its unreserved efforts to deliver quality education, Dr. Lemma said.



He also added that the training helps the university's academic community to raise their awareness in the area of standardization and authentication. Following the recent differentiation made by the Ministry of Education, ECSU has been differentiated as a Research University and has planned to accredited all the programs of the university in the coming few years and cope up the challenges in relation to the quality of Education it delivers.

Finally he requested the trainees to actively participate on the training and implement it in their teaching learning activities.

Education Training Authority Deputy Director Dr. Dinkuana Neggussa and his team gave detailed training on Quality and Quality Enhancement concepts and practice in higher education, program Standardization and Accreditation and Sources of Data for Accreditation. On the training it is noted that educational institutions mainly in Ethiopia need transparency and it is important to measure the capabilities of students in well-defined and known standard. It is also emphasized to make the issue of Quality education the main agenda of the higher institutions. Participants of the training on their part, raised different questions and ideas in connection with the issues of quality and how it is measured and held a detailed discussion on it.



# ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆን ለዩኒቨርሲቲዎች ትልቅ ዕድል እንጂ ስጋት አለመሆኑ ተገለጸ፡

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የአካዳሚክ የኮሌጅ ዲኖች፣ ምክትል ዲኖችና የትምህርት ክፍል ኃላፊዎች ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን እያደረገ ባለው የሽግግር ወቅት ተግባራት እና ዩኒቨርሲቲው እስካሁን ባደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ላይ ጥር 23 ቀን 2016 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ በተደረገው ውይይት የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆን ለዩኒቨርሲቲዎች ትልቅ ዕድል እንጂ እንደ ስጋት ሊወሰድ እንደማይገባው ገልጸዋል።

በውይይቱ መክፈቻ ላይ ፕ/ር ፍቅሬ በሰጡት ማብራሪያ መድረኩ ቀደም ሲል የተጀመረው የለውጥ ስራዎች ላይ ያለውን የሀሳብ ግልጽነት የሚያስፈልጋቸው ሀሳቦች እንዲሁም በቀጣይነት የሚሰሩ ስራዎች ላይ ግልጽነት ለመፍጠር የተዘጋጀ መድረክ መሆኑን ጠቅሰው እንደ ሀገር የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች በቀጣዩ ሶስት ዓመታት ውስጥ ወደ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲነት እንዲገቡ በተቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ከ2016 ዓ.ም ጀምሮ የሽግግር እቅድ አዘጋጅተን እየሰራን እንገኛለን ብለዋል። አሁን እየተሰራ ያለው ሥራ አስመልክቶ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆን ለዩኒቨርሲቲው ምን የተለየ ጥቅም ይኖረዋል ከሚል ሀሳብ ጋር አያይዘው ራስ-ገዝነት ዩኒቨርሲቲያችንን የበለጠ የማብቃት፣ ራስን በራስ ያለማንም ጣልቃ ገብነት የማስተዳደር እና በነጻነት የሚንቀሳቀስበት በአዋጅ በሚሰጠው ስልጣን እና የራሱ የሆነ የህግ ማዕቀፍ ተዘጋጅቶለት እንዲንቀሳቀስ የሚያስችለው በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የበለጠ አቅም የሚያገኝበት ፣ የላቀ ስራዎችን እንዲሰራና ተልዕኮውንም በተሳካ ሁኔታ እንዲወጣ አቅምንና ዕድልን የሚሰጥ መሆኑን አብራርተዋል።





ፕ/ር ፍቅሬ አክለውም ራስ-ገዝነት ተቋማዊ ነጻነትና ስልጣን የሚሰጥ በመሆኑ አሁን ያለውን መዋቅር በራሱ ከልሶ በሚያዋጣው መልኩ የመቀየር እና የማሻሻል ብሎም ዩኒቨርሲቲውን የሚመሩ አካላትን እስከመሰየም የሚያችል አቅምንና ስልጣንን የመስጠት እንዲሁም የአካዳሚክ ነጻነትን በመስጠት ዩኒቨርሲቲው የራሱ የሆነ የተማሪዎች ምልመላና ቅበላ ፖሊሲ በማዘጋጀት በራሱ መስፈርት ተማሪዎችን የመቀበል መብት እና በየትምህርት ክፍሎች የሚኖሩ የተማሪዎች ቁጥር የመወሰን፣ የትምህርት ፕሮግራሞችንም

ያለማንም ይሁንታና ጣልቃገብነት ተፈላጊነትንና ተመራጭነታቸውን በመመዘን በራሱ የመቅረጽ መብትና ስልጣን ብሎም የትምህርትና የስልጠና ጥራትን ለማረጋገጥ የራስ የሆነ ማዕቀፍእንዲኖር ነጻነትንየሚሰጥ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡ ራስ-ገዝነት በሚሰጠው የሰውሀብትን የማስተዳደር ነጻነትንም ለዩኒቨርሲቲው የሚያስፈለገውን የሰው ኃይል ቅጥር፣ የደረጃ ዕድገትና የመሳሰሉትን በራስ መስፈርትን በመከተል ማከናወን የሚያስችል መብትን፣ በሚኖረው ፋይናንስ ነጻነትም የራስን ገቢ ማመንጨትና የመጠቀም መብትን የሚሰጥ ነው፡፡ በዚህም ተቋሙ ዓላማውን ለማሳካት እስከአስቻለው ድረስ በተለያዩ የገቢ ማመንጫ ዘርፎች ላይ በመሰማራት ገቢን በማመንጨት እና በራስ በመንቀሳቀስ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከመንግስት ጥገኝነት የሚላቀቅ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት እስከ 2018 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲው እስከ ሃያ በመቶ ድረስ በራሱ በጀት ለመጠቀም ግብ መቀመጡን ይንንምለማሳካትበዩኒቨርሲቲውበጠቅላላውሃያየገቢማመንጫዘርፎችተለይተውእየተሰራባቸውመሆኑንፕሬዚዳንቱገልጸዋል፡፡



ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆኑ በራሱ ጥራት ያለው ትምህርና ስልጠና ለመስጠት፣ ያለን ሀብትን ያለብክነት በጥንቃቄ ለመጠቀም እና ተመራጭና ተወዳዳሪ የትምህርት ፕሮግራሞች እዲኖሩ ዕድል የሚሰጥ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን በዋናነት ጠንካራ የሰው ኃይል ፣ ጠንካራ የሆነ የፋይናንስ አቅም እንዲሁም መሰረተ-ልማት መኖር ወሳኝ ጉዳይ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲውም ከ2016 ዓ.ም መጀመሪያ ጀምሮ እስካሁን የተደረገው ጥረት ሲያብራሩም የሰው ኃይሉን በተመለከተም በቂና ብቁ የሆነ የሰው ኃይል መኖር ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን አንዱና ወሳኝ ጉዳይ ከመሆኑ አንጻር በዚህ የሽግግር ወቅትም በዩኒቨርሲቲው የሚገኙ የአካዳሚክ ሰራተኞች ፕሮፋይል ማደረጀት ትልቅ ትኩረት የሚሰጠዉ መሆኑን አስታውሰው በዚህም ሰራተኛው ያለው የትምህርት ዝግጅት፣ ያካበተው ልምድ ፣ በምርምርና በህትመት ላይ ያለው ተሳትፎና አቅም ተመዝኖ ምን ያህል ብቁ እንደሆነ የሚመዘንበት አሰራር እየተተገበረ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በውይይት መድረኩም አዲስ በተዘጋጀው የሰራተኞች ፕሮፋይል መሙያ ቅጽ ላይና በአጠቃላይ ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ ጋር የተያያዙ ሀሳቦችንና ጥያቄዎች የቀረቡ ሲሆን ፕ/ር ፍቅሬም ለተነሱት ሀሳቦችና ጥያቄዎች ዝርዝር ማብራርያን ሰጥተዋል፡፡ በማጠቃለያቸውም ላይ የዩኒቨርሲቲው ዕጣ ፋንታ በሰራተኞች እጅ ላይ ያለ መሆኑን አጽንኦት ሰጥተው በዚህ የሽግግር ወቅት በትጋት በመስራትና ራስን በማብቃት ብቁና ተወዳደሪ ሆኖ መገኘት እጅግ ወሳኝ በመሆኑ ሁሉም ሰራተኛ በታላቅ የኃላፊነት ስሜት መስራት እንደሚገባው አሳስበዋል፡፡

# የኢሲሰዩ የመኖሪያ ቤት ተጠቃሚ ሰራተኞቹ የምስጋና ፕሮግራም አደረጉ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ሁለት G+ 10 ህንጻ 175 አባወራዎችእና እማወራዎች የሚዝ በማስገንባት ለመምህራን እና ለሰራተኞች ማስረከቡ ይታወቃል ፡ይህንንም ትልቅ ተግባር ላበረከቱ አመራሮች ነዋሪዎች የምስጋና ፕሮግራም በማዘጋጀት በ 9/6/2016 ዓ.ም ምስጋና አቅርበዋል።

በምስጋና መክፈቻ ፕሮግራም ላይ የነዋሪዎች ተወካይ ዶ/ር ደጀኔ ግርማ እንዳሉት ይህ ትልቅ ሸክም በማቅለል፣ የሰራተኛዉን የቤት ችግር ጥያቄ በመቀበል ፣የግንባታዉን ሀሳብ ጭምር በማመንጨት ለሰራተኛዉ ፈጣን ምላሽ በመስጠት ብዙ ዉጣ ዉረዶችን በማለፍ ለዚህ ልዩ ቀን ላደረሱን ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ነዋሬዎችን ወክዬ ምስጋና በማቅረቤ ትልቅ ደስታ ይሰማኛል ብለዋል። እንዲህ አይነት ምቹ ሁኔታ የተቋሙ ሀላፊዎች በመፍጠራቸዉ ሠራተኛዉን በስራዉ አካባቢ ተረጋግቶ መስራት የሚያስችል፣ ያለበትንም ጫና የሚቀንስ እና የተሰጠዉን ሀላፊነት በተሳካ ሁኔታ ለመፈጸም የሚያስችል ልዩ ፕሮጀክት ሲሆን ፕሬዚዳንቱ ተቋሙን ለመምራት በተቀላቀሉን ወቅት የሰራተኛዉ የቤት ችግር ጥያቄ ያቀረብን ሲሆን ለዚህም ምላሽ ፕሮጀክት ቀርጸዉ ብዙ ዉጣ ዉረዶችን አልፈዉ ሰራተኛዉ በቤቱ እንዲኖር ትልቅ አስተዋጽኦ ላደረጉት ለዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት አሁንም ደግመን ደጋግመን እናመሰግናለን በማለት የኛ ምስጋና የአንዴ ብቻ ሳይሆን ሁሌም በወጣን በገባን ቁጥር ምስጋናችን በልባችን እናቀርባለን ለዚህም የነዋሪዎች ኮሚቴ ይህንን የምስጋና ፕሮግራም ያዘጋጀዉ ብለዋል።



የዩኒቨርስቲዉ ፕሬዚዳንት ፕ/ር ፍቅሬ በዕለቱ የተሰማቸዉን



ደስታ በመጥቀስ ይህ ፕሮጀክት ብዙ ዉጣ ዉረዶች የታለፈበት ቢሆንም የልፋታችን ዉጤት በዚህ መልኩ ስናየዉ ደስታችን የላቀ ፣ድካማችንን ያስረሳ ስኬት ሲሆን አሁን እንዲህ ሰራተኛዉ ገብቶ መኖር በመጀመሩ ለኔ ልዩ ስሜት ያለዉ ሲሆን ከሰራኋቸዉ ስራዎች፣ በህይወቴ ከተደሰትኩባቸዉ ቀናቶች በሙሉ ትልቁን ቦታ ይይዛል ብለዋል። በህይወት ዘመን ብዙ የግል ስኬቶች ቢኖሩም ነገር ግን በተለይ ለሌላዉ ሰዉ ነገሮችን ማመቻቸት ኑሮን ማቅለል የመሰለ ደስታ የሚሰጥ ሀላፊነት የለም በማለት ለዚህች ልዩ ቀን ደርሰን እናንተም ተደስታችሁ ስላመሰጋናችሁን በማናጅመንቱ ስም አመሰግናለዉ ብለዋል። በተጨማሪ ለዚህ ፕሮጀክት መሳካት ያላሰለሰ ጥረት ላደረጉ ሰራተኞች ፣አመራሮች እኔም የላቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ብለዋል ። በመጨረሻም ኮሚቴዉ የምስጋና ሽልማት እና እዉቅና ሰርተፍኬት በመስጠት ፕሮግራሙ ተጠናቋል።ይህ ፕሮጀክት ሁለት G+ 10 ሕንጻ ያሉት በአጠቃላይ 175 አባወራዎችእና እማወራዎች የሚኖሩበት ዘመናዊ የመኖርያ መንደር ነዉ።



# ኢሲሰዩ ባለ ስምንት ወለል አዲስ ህንጻ ለማስገንባት ውል ተፈራረመ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ አዲስ ለሚያሰራው ባለ ስምንት ወለል ህንጻ ፕሮጀክት ባወጣው ጨረታ መሰረት የጨረታው አሸናፊ ከሆነው ጉተማ ፈሬሳ ኮንስትራክሽን ጋር መጋቢት 10 ቀን 2016 ዓ.ም የግንባታ ማስጀመርያ ስምምነት ውል ተፈራረመ።



በስምምነት ፊርማ ስነ-ስርዓቱ ወቅትም የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ እንደገለጹት ይህ አዲስ የሚገነባው ባለስምንት ወለል ህንጻ በዩኒቨርሲቲው የመጀመሪያ ሊባል የሚችል እስካሁን ካከናወናቸዉ ፕሮጀክቶች ትልቁ ፕሮጀክት ሲሆን በተለይ ተቋሙ ራስ ገዝ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንደአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ሊይዛቸዉ የሚገቡ ዘመናዊ መማሪያ ክፍሎች ዘመኑ የደረሰባቸዉ ቴክኖሎጂዎች አደራጅቶ ይይዛል ብለዋል፡ ፡ ህንጻዉ ሲጠናቀቅ በርካታ አገልግሎት የሚሰጥ ዘመናዊ ክፍሎች ለተለያየ አገልግሎት የሚዉሉ ዘመኑ ባፈራቸዉ ቴክኖሎጂ የታገዙ ዘመናዊ የዉስጥ ቁሳቁሶች አብሮ ያካተተ ሲሆን ለዩኒቨርስቲያችንም እንደ አንድ ''ላንድ ማርክ'' ተደርጎ የሚወሰድ ነዉ ብለዋል። ተቋራጩም ባለው የካበተ ልምድ እና ቀደም ሲልም በዩኒቨርሲቲው ሌሎች ህንጻዎችንም በገባው ውል መሰረት አጠናቆ ያስረከበ ድርጅት እንደመሆኑ መጠን ይህን ፕሮጀክትም በውሉ መሰረት አጠናቆ እንደሚያስረክብ ሙሉ እምነት እንዳላቸዉ በመግለጽ ፤ነገር ግን በተቻለ መጠን በተቀመጠዉ ግዜ ሰሌዳ አጠናቆ ለአገልግሎት እንዲደርስ፣ ተቋሙ የጀመረዉ የራስ ገዝ ሂደት የሚያፋጥን ስለሚሆን አደራ እያልን ድርጅቱም ሀገራዊ ሀላፊነቱን እንዲወጣ እንጠይቃለን ብለዋል።

የጉተማ ፈሬሳ ኮንስትራክሽን ሥራ አስኪያጅ አቶ ጉተማ ፈሬሳ በስምምነቱ የተሰማቸው ደስታ ገልጸው ፕሮጀክቱን በውሉ መሰረት በማጠናቀቅ ለዩኒቨርሲቲው ለማስረከብ ያላቸውን ቁርጠኝነት ገልጸው ከዩኒቨርሲቲውና ከአማካሪ ድርጅቱ ጋር በመነጋገር፣ በመወያየትና በመተጋገዝ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንደሚሆን ቃል ገብተዋል። የፕሮጀክቱ አማካሪ ኡቦን ቨያጅ አማካሪ ድርጅት ሀላፊ አቶ አለሙ መረራ በበኩላቸው ፕሮጀክቱ ሁሉን አካታችና ዘመናዊ ህንጻ ከመሆኑ እና ስምምነቱም ህንጻውን ከነሙሉ ግብዐቱ አጠናቆማስረከብንየሚያካትትበመሆኑከተለመደውየግንባታ አካሄድ ወጣ ያለ መሆኑን ተገንዝቦ አሸናፊዉ ድርጅት ከወዲሁ በሁሉም ረገድ ብቁ ሆኖ መገኘት ተገቢ መሆኑን አሳስበዋል። የፕሮጀክቱን አጠቃላይ ሂደት በተመለከት የኢሲሰዩ የምህንድስናና ጥገና አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ አቶ አለሙ ሲሳይ እንደገለጹት ይህ ሁለገብ የመማርያ ህንጻ ለመገንባት ግልጽ ጨረታ የወጣ ሲሆን የተለያዩ ተወዳዳሪዎች ተወዳድረዉ 5 ተወዳዳሪዎች የተቀመጠዉን መስፈርት ያሟሉ ሲሆን ከእነዚህ ዉስጥም የጉተማ ፈሬሳ ኮንስትራክሽን ድርጅት በ 2,326,162,955.48 (ሁለት ቢሊየን ሶስት መቶ ሀያ ስድስት ሚሊየን አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺ ዘጠኝ መቶ አምሳ አምስት ብር ) እንዳሸነፈ አብራርተዋል።

የሚገነባው ሕንጻም እጅግ ዘመናዊ መሆኑ የጠቀሱት አቶ



አለሙ በውስጡም 19 የተለያዩ ቢሮዎችን፣ 24 አንድ መቶ ተማሪዎችን የሚይዙ የመማሪያ ክፍሎችን፣ 18 ሰላሳ ሰዎችን የሚይዙ ስማርት ክፍሎችን፣ 285 እና 110 ሰዎችን የሚይዙ ሁለት አዳራሾችን ፣ 11 ሱቆችን፣ 1 ሺ ተማሪዎችን በአንድ ጊዜ የሚያስተናግድ አንድ ቤተ-መጽሐፍ፣ 6 ተማሪዎች እርስ በርስ የሚወያዩባቸው ስቱደንት ኮርነርስ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዙ ፣ 87 መኪናዎችን በአንድ ጊዜ ማቆም የሚያስችል የመኪና ማቆሚያና ሌሎች አገልግሎቶችን የሚሰጥ ህንጻ መሆኑን ገልጸዋል።



# ኢሲሰዩ ካውንስል የ2016 የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን ግምገማ አካሄደ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ካውንስል የዩኒቨርሲቲውን የ2016 ዓ.ም የዘጠኝ ወራት የስራ ክንውን እና መደበኛ የሪፎርም ስራዎች አፈጻጸም ግምገማ ሚያዝያ 4 ቀን 2016 ዓ.ም በህዳሴ አዳራሽ አካሄደ።



በግምገማ መድረኩ መክፈቻላይ የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚደንት ፕ/ር ፍቅሬ ደሳለኝ ባደረጉት ንግግር መድረኩ ያለፉትዘጠኝ ወራት በሪፎርምና በዕቅድ የተያዙ ሥራዎች ክንውንየሚገመገምበት እና በቀጣይ ለሚተገበሩ ሥራዎችም አቅጣጫ የ ም ና ስ ቀ ም ጥ በ ት መድረክ ነው ብለዋል፡ ፡ አክለውም ከ2016 ዓ.ም የበጀት ዓመት ጀምሮ የተሟላ የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆንና የተሸለ መዋቅራዊ፣ አስተዳደራዊና አካዳሚያዊ ነጻነትን ሊያጎናጽፈን የሚችለውን ራስ-ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆንን የሚያስችል የዝግጅት ጊዜ ዕቅድ አቅደን እየሰራን የቆየን በመሆኑ በዚህ ረገድ የተሰሩ ሥራዎችን በዝርዝር የምንገመግምበት፤ አጀንዳዎቹም ሰፋፊና በርካታ ጉዳዮችን ያካተቱ በመሆናቸው እየተተገበሩ ያሉትን ሥራዎች ከምን ላይ እንደደረሱ ካዉንስሉ የሚያረጋግጥበት መድረክ ነው ብለዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞም የምርምር ዩኒቨርሲቲ መሆን እና ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ መሆን እራሳቸውን የቻሉ ሁለት የተለያዩ አጀንዳዎች መሆናቸው የገለጹት ፕ/ር ፍቅሬ በምርምር ዩኒቨርሲቲነት የተቀመጡትን ሀገራዊ መስፈርቶች በሚገባ ማሟላት ወሳኝ መሆኑን ፣ ራስ-ገዝ ዩኒቨርቲነትም የሚፈለገውን መስፈርት ተሟልቶ ሲገኝ ብቻ የሚገኝ መሆኑን ጠቁመው ባለፉት ዘጠኝ ወራት የተከናወኑ ተግባራትን ከእነዚህ መስፈርቶች አኳያ በስፋት እንገመግማለን ብለዋል።



እነዚህን አጀንዳዎች ለመተግበርም ለዩኒቨርሲቲው በተፈቀደው የምርምር ዩኒቨርሲቲ መዋቅር መሰረት የሰራተኞች ምደባ መደረጉ ትልቁን መደላድል የፈጠረ እና ከዚህ ጋር ተያይዞ የመጣው ለውጥ ምን እንደሆነ፣ ለተልዕኮ ስኬት እጅግም ረብ የማይኖራቸውን ለማጥራት በቀጣይ የሚሰራበት ጉዳይ መሆኑን ያወሱት ፕ/ር ፍቅሬ በስፋት አዲስ ከተተገበረው መዋቅር ጋር ተያይዞ የሴኔት መተዳደሪያና የተከታታይ ትምህርት መመሪያ ብቻ የተሻሻሉ በመሆናቸው በቀጣይ ሌሎች በርካታ መሻሻል ያለባቸው ደንቦች ፣ መመሪያዎችና ፖሊሲዎች መታየት እንደሚኖርባቸው በአጽንኦት አሳስበዋል።

ራስ-ገዝ መሆንን አስመልክቶም ራስ ገዝነት ''ራስን በራስ ማስተዳደር'' ማለት ሳይሆን ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን የፋይናንስ አቅም ማሳደግ የተለያዩ የገቢ ምንጮቹን በመለየት ወደ ትግበራ በመግባት ገቢ ማመንጨት፣ ተያያዥ የአፈጻጸም ነጻነቶች ማግኘት ነዉ ብለዋል። ራስን በራስ ማስተዳደር ያለበቂ ሀብት የማይታሰብ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ጠንካራ የፋይናንስ አቅም እንዲኖረው ለማስቻል 22 የተጠኑ የገቢ ማመንጫ ተለይተው እየተሰራባቸው መሆኑን፣ እና ሌሎችም በማጠናከር በ2020 ዓ.ም 30 በመቶ የራሳቸውን በጀት ከውስጥ ገቢ ለመሸፈን የተጣለውን ግብ ለማሳካት መትጋት ያስፈልጋል። ሌላው ብቁና በቂ የሰው ኃይል መኖር፣ ያሉት የትምህርትና የስልጠና ፕሮግራሞች ተፈላጊነት፣ የተማሪዎች ምልመላና ቅበላ ፖሊሲዎች፣ የትምህርትና ስልጠና ጥራትን ማስቀጠል፣ ጠንካራ የምርምርና የማማከር ስርዓትን መፍጠር፣ በድህረ ምረቃ የሚሰራ የምርምር ውጤት

በአግባቡ ማደራጀት፣ የዲጂታል የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ማጠናከር፣ በትብብርና ትስስር እንዲሁም ዓለማቀፋዊነት አንጻር እየተሰሩ ያሉ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም እና ውጤቶች፣ ደረጃውን የጠበቀ የመሰረተ ልማት እና ፋሲሊቲ ማስፋፋት እና ሌሎች አንኳር ጉዳዮች ላይ የተሰሩና የታዩ ጉድለቶችን በማንሳት መወያየት እንደሚገባ አስምረውበታል፡፡ አያይዘውም ዩኒቨርሲቲው ባለፉት ዓመታት በኦዲት ግኝት ያልተገኘበት ተቋም መሆኑን አስገንዝበው ይህ ጠንካራ የኦዲት ስርዓት ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት መሆኑን ለካውንስሉ ገልጸው የበጀት እጥረት፣ ለተማሪዎች በሚቀርበው የምግብ አቅርቦት እና ሌሎችም ውጫዊ ጉዳዮች ጫና የፈጠሩበት መሆኑን ለካውንስሉ ገልጸዋል፡፡



በማስከተልም በአራቱ ዘርፍ ማለትም በአካዳሚክ ጉዳዮች ም/ፕሬዚዳንት ፣በምርምርና ትብብር ዘርፍ ም/ ፕሬዚዳንት፣በማናጅመንት ዘረፍ እና በአስተዳደር እና ልማት ም/ፕሬዚዳንት ዘርፍ የተከናወኑ የየዘርፋቸውን የዘጠኝ ወራት የሥራ ክንውን እና የሪፎርም ሥራዎች ሪፖርት ለካውንስሉ ያቀረቡ ሲሆን ከቀረበው ሪፖርት መሰረትም የሪፎርም ስራዎችን በተመለከተ ከራስገዝነት ተልዕኮ ልየታ፣ በመረጃ አያያዝና ዲጂታል ሥርዓት ግንባታን በተመለከተ IFMIS፣ ICSMIS፣ EGP፣የCCTV ካሜራና የሠራተኞች ቁጥጥር በጣት አሻራ ቴክኖሎጂዎች ማካሄድ መቻሉን ፣ አዳዲስ የካሪኩለም ማሻሻያዎች፣ የትምህርት ጥራትንለማሻሻል፣እናየሰውኃይልንምበበቂሁኔታለማብቃት የተለያዩ ስራዎች መሰራታቸውና ስልጠናዎች መሰጠታቸው በሪፖርት ቀርቧል፡፡ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ደንቦች መከለሳቸው፣ የሚሰሩ የምርምር ጭብጦች የተለዩ መሆናቸው፣የተጀመሩአጋርነቶችንወደተሻለደረጃእንዲያድጉ መደራጀታቸው በተለይ ዩኒቨርሲቲው የጎረቤት ሀገራትን ሲቪል ሰርቪስ ግንባታ ለመደገፍ እና ትብብርን ለማጠናከር እየሰራ ያለዉ ስራ በዝርዝር የቀረበ ሲሆን የዓለም አቀፍ ተማሪዎችና መምህራን በተቋሙ ተሳትፎአቸዉ አሁን ካለበት ደረጃ ከፍ ማለት እንደለበት ተመላክቷል ፤ በ 2015 ዓ.ም ፋይናንስ ከተደረጉ ምርምር ስራዎች አስራ ሁለቱ መታተማቸው ከ2011 እስከ 2015 ዓ.ም የተካሄዱ አመታዊ የምርምር ጉባኤዎች ላይ የቀረቡ የጥናት ወረቀቶች በተቋሙ ድረ ገጽ ላይ መጫናቸው እና በማማከር አገልግሎትም ጥራትና ብዛትን ለማሻሻል የተለያዩ ስራዎች መሰራታቸው በሪፖርቶቹ ተመላክተዋል፡፡

አስተዳደርና ልማትን በተመለከተም ዩኒቨርሲቲው ባካሄደው ሰራተኞች ምደባ ለ 979 ሰራተኞችን በአዲሱ መዋቅር መሰረት ሁሉም ሰራተኞች በሚባል ደረጃ በአሁኑ ወቅት ላይ ምደባ ማግኘታቸው ተገልጸዋል፡፡ የበጀት፣ የፋይናንስ፣ የግዥና የንብረት አስተዳደርን አስመልክቶም በርካታ ስራዎች መከናወናቸው በሪፖርቱ የተገለጸ ሲሆን ባለፉት ዘጠኝ ወራት 37,108,671.57 ብር ከወጪ ቀሪ የውስጥ ገቢ መገኘቱ፣ አጠቃላይ የበጀት አጠቃቀሙም 82.25 በመቶ መሆኑ እንዲሁም ደረጃቸውን የጠበቁ መሰረተ ልማትና ፋሲሊቲዎች ማደረጃትን በተመለከተ በአዲስ አበባ ዋናው ግቢ በተለይ ትምህርትና ስልጠናን በዘመናዊ መንገድ የሚያስኬዱ G+7 የስልጠና ማዕከል እና G+8 ሁለገብ ሕንጻዎች ግንባታ እያካሄደ መሆኑን በተጨማሪም ነባር የወሊሶ ካምፓስ ግንባታዎች እየተካሄዱ መሆኑ ተገልጿል፡፡ በተጨማሪም በ2015 መጨረሻ ተግባራዊ ለተደረገዉ የመጀመሪያ ዲግሪ የመዉጫ ፈተና (Exit Exam) ለሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች በኢሲሰዩ ዉስጥ የተዘጋጀ ሲሆን ተገቢዉን ግብዓት በማቅረብና በማስተባበር እንዲሁምየሌሎችተቋማትተማሪዎችጭምርበዩኒቨርሲቲዉ እንዲፈተኑበማመቻቸትረገድዩኒቨርሲቲዉተቋማዊሀላፊነቱን በብቃት በመወጣት ጉልህ ሚና እንደተጫወተ ተገልጿል፡፡

የካውንስሉ አባላትም በቀረበው ሪፖርት ላይ የተለያዩ ጥያቄዎች፣ ሀሳብና አስተያየቶችን እንዲሁም መስተካከል የሚገባቸው ጉዳዮችን በማንሳት ሰፊ ውይይቶችን ሲያደረጉ አባላቱ ላቀረቧቸው ጥያቄዎችና አስተያየቶችም የየዘረፉ ኃላፊዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል፡፡

በማጠቃላያዉም ላይ ፕሬዚዳንቱ እንዳሳሰቡት በተለይ እንዲህ አይነት ግምገማ እነደ አመራርም ትልቅ ትኩረት የምንሰጠዉ ፤ የካዉንስል አባላትም በግልጽነት ጥያቄዎች እና ማብራሪያዎች የሚያነሱበት እና የምንወያይበት መድረክ እንደመሆኑ የካዉንስል አባላት በስብሰባ በመገኘት ሀላፊነታቸዉን መወጣት አለባቸዉ ብለዋል፡፡ በመጨረሻም ለአራተኛ ሩብ አመት አቅጣጫ በማስቀመጥ የዕለቱ ግምገማ ተጠናቋል፡፡

# የዩኒቨርሲቲው አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶች በተመለከተ ከአቶ አለሙ ሲሳይ ጋር የተደረገ ቃለ-መጠይቅ

የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር በቅርቡ ባደረገው ልየታ መሰረት በምርምር ዩኒቨርሲቲነት መመደቡን ተከትሎ የተለያዩ የለውጥ ሥራዎችንና የመሰረተ ልማት ማስፋፊያ ፕሮጀክቶችን አቅዶ ወደ ተግባር መግባቱ ይታወቃል። በቅርቡም ዩኒቨርሲቲው ራስ ገዝ ዩኒቨርሲቲ ለመሆን በሚያደርገው ጥረትም የእነዚህ የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች የሚኖራቸው አስተዋጽኦ እጅግ ከፍተኛ እንደሚሆን ይታመናል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ስለ ፕሮጀክቶቹ አጠቃላይ ሁኔታና የግንባታ ሂደት አስመልክቶ ከዩኒቨርሲቲው የምህንድስና አገልግሎት ሥራ አስፈጻሚ አቶ አለሙ ሲሳይ ጋር አጭር ቆይታ አድርገናል። መልካም ቆይታ።

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ

*በመጀመሪያ ለቃለምልልሱ ፈቃደኛ ስለሆኑ ከልብ እናመሰግናለን።*

አቶ አለሙ፡

እኔም እንግዳችሁ ስላደረጋችሁኝ አመሰግናለሁ።

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ

ዩኒቨርሲቲው በዕቅድ ይዞ እየተገበራቸው ያሉትን አዳዲስና ነባር የማስፋፊያ ፕሮጀክቶች ምን ምን እንደሆኑ ቢገልጹልን ?

አቶ አለሙ፡

በዕቅድ ይዘን እየተገበርናቸው ያሉ ፕሮጀክቶች በመጀመሪያው ዙር የአካዳሚ ህንጻ፣ የሰልጣኞች ማደርያ የሚሆን ዘመናዊ ሆስቴል፣ ዘመናዊ ማብሰያ ኪችን፣ የአፈር ምርመራ ላቦራቶሪ እና ከጥልቅ የውሃ ጉድጓድ ግንባታ ጋር የተያያዙ የመሰረተ ልማት ሥራዎች ሲሆኑ ከእነዚህ ውስጥ የተወሰኑት ወደ ማጠናቀቂያ ደረጃ የደረሱ ናቸው።

በሁለተኛ ዙር አሁን እየተተገበሩ ያሉት ደግሞ ባለ ሰባት ፎቅ የስልጠና ማዕከል እና ባለ ስምንት ፎቅ የትምህርት ክፍሎች ናቸው። ሌላው በሚቀጥለው ዓመት ወደተግባር የሚገባበት ባለ አስር ወለል የተማሪዎች ማደሪያ እና መመገቢያ ካፌን የያዘ ህንጻ ነው።

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ

*እነዚህ ፕሮጀክቶች በውስጣቸው ምን ምን ክፍሎችን እንዳካተቱና ሲጠናቀቁም የሚሰጧቸውን አገልግሎቶች በዝርዝር ቢነግሩን*

አቶ አለሙ፡

አንደኛው በ566 ካሬ ላይ ያረፈ ባጠቃላይ 4030 ካሬ ስፋት ያለው ባለ ሰባት ወለል የስልጠና ማዕከል ሲሆን የሚጠይቀውም በጀት ብር 687,299,720.41 (ስድስት መቶ ሰማንያ ሰባት ሚሊዮን ሁለት መቶ ዘጠና ዘጠኝ ሺህ ሰባት መቶ ሃያ ብር ከአርባ አንድ ሳንቲም) ነው፡፡ በአንድ ጊዜ ከሃምሳ እስከ ስልሳ ሰው ማስተናገድ የሚችሉ ሃያ ዘጠኝ ስማርት የስልጠና ክፍሎችን የያዘ ፣ በድምሩ በአንድ ጊዜ አንድ ሺህ አምስት መቶ ሰው ማስተናገድ የሚችል ህንጻ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በምድር ወለል (ግራውንድ) ላይ 135 ካሬ ዩኒቨርሲቲው እራሱን የሚያስተዋውቅበት ጋለሪ (ሙዚየም) ፣ አንደኛ ወለል ላይ 74 ካሬ ለሻይ ቡና አገልግሎት የሚውል ኦፕን ኪችን ያካተተ ዘመናዊ ህንጻ ነው።

ወደ ሁለተኛው ባለ ስምንት ፎቅ አካዳሚክ ህንጻ ስንመጣ የመማሪያ አገልግሎት የሚሰጥ ህንጻ ሲሆን፣ የሚጠይቀውም በጀት ብር 2,326,162,955.48 (ሁለት ቢሊዮን ሶስት መቶ ሃያ ስድስት ሚሊዮን አንድ መቶ ስልሳ ሁለት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሃምሳ አምስት

ብር ከአርባ ስምንት ሳንቲም) ነው። ህንጻው ያረፈው በ2004 ካሬ ቦታ ላይ ሲሆን፣ በአጠቃላይ 15410 ካሬ ስፋት ይኖረዋል። የሚሰጣቸው አገልግሎቶች ሲዘረዘሩ፣ እያንዳንዳቸው 25 ካሬ ስፋት ያላቸው ሃያ አምስት ሰው



መያዝ የሚችሉ ሰባት ፑል ቢሮዎች፣ እያንዳንዳቸው 10 ካሬ ሜትር ስፋት ያላቸው አስራ ሁለት ነጠላ (Single type) የሰራተኛ የጋራ ቢሮዎች፣ እያንዳንዳቸው በአንድ ጊዜ አንድ መቶ ሰው ማስተናገድ የሚችሉ ሃያ አራት የመማሪያ ክፍሎች፣ እያንዳንዳቸው 30 ካሬ ስፋት ያላቸው በአንድ ጊዜ ሰላሳ ሰው ማስተናገድ የሚችሉ ስማርት የመማሪያ ክፍሎች፣ 1110 ካሬ ስፋት ያለው ትልቅ ላይብራሪ፣ ተማሪዎች አሳይመንት እና ፕሮጀክት በጋራ የሚሰሩበት ዋይፋይ እና ዳታ ያለው 6 የተማሪዎች ጥግ (Student Corner)፣ አንድ 280 ሰው ማስተናገድ የሚችል ትልቅ የመሰብሰቢያ አዳራሽ፣ አንድ መካከለኛ 110 ሰው ማስተናገድ የሚችል አዳራሽ ተካቶበታል። በተጨማሪም ለንግድ አገልግሎት የሚውሉ 11 ሱቆች አሉት፤ ከዚህ ሌላ ህንጻው ባለ ሶስት ቤዝመንት ሲኖሩት አንዱ ብዝመንት ለፓርኪን አገልግሎት የሚውል እና በአንድ ጊዜ 90 መኪና የመያዝ አቅም ያለው ነው። በተጨማሪም በአንድ ጊዜ 1600 ተማሪዎችን ማስተናገድ የሚችል ሬስቶራንት እና ካፌ አካቶ የያዘ በዓይነቱ ልዩ የሆነ ዘመናዊ እና በዩኒቨርሲቲው ታሪክም ልዩ የሆነ ህንጻ ነው።

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ

ፕሮጀክቶቹ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ተብሎ ታቅዷል?

አቶ አለሙ:-

እንግዲህ በእቅዳችን እና በውላችን መሰረት ሁለቱም ህንጻዎች በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ የሚጠናቀቁ ናቸው፤ እኛም በዚሁ ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃሉ ብለን እንጠብቃለን።

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ

ዩኒቨርሲቲው ራስ-ገዝ ለመሆን ከሚያደርገው ጥረት እና እየተገበረው ካለው ሪፎርም አኳያ ፕሮጀክቶቹ ምን አስተዋጽኦ ይኖራቸዋል?

አቶ አለሙ:-

በትምህርት ሚኒስቴር በተደረገው ልየታ መሰረት ዩኒቨርሲቲያችን የምርምር ዩኒቨርሲቲ ተብሎ ተለይቷል። ከዚህ በተጨማሪም በሶስት አመት ጊዜ ውስጥ ራስ-ገዝ መሆን ይጠበቅበታል። ስለዚህ እነዚህን የመሰረተ ልማት ስራዎች ስናከናውን ከዚህ አላማ ጋር የተመጋገቡ እንዲሆኑ በማሰብ ነው። እነዚህ ልማቶች የዩኒቨርሲቲውን የማስተማር እና የማሰልጠን አቅም የሚጨምሩ ናቸው። ዘመኑ የሚጠይቀውን ቴክኖሎጂ የሚያሟሉ ስለሆኑ ተመራጭ ያደርጉናል። ሆስቴላችን በአንድ ጊዜ 120 ሰልጣኞችን ያስተናግድልናል፤ የንግድ ማእከላቱም ተጨማሪ ገቢ ያስገኙልናል። ሌላው አሰራራቸው በጣም ዘመናዊ ስለሆነ ለማስተማርም ለኪራይም ያገለግላሉ። ከዚህ ጋር አብሮ የሚጠቀስ በአንድ ጊዜ 100 ሰው የሚያስተናግድ ጂምናዝየምም አብሮ ተገንብቷል። እነዚህ ሁሉ ተደማምረው ለዩኒቨርሲቲው የሚፈጥሩት አቅም ከፍ ስለሚል፣ ዩኒቨርሲቲው በታቀደለት ጊዜ ራስ-ገዝ ሲሆን ሊያጋጥመን የሚችለውን የበጀት እጥረት ያቃልላሉ ተብሎ ይታሰባል። ስለዚህ ዩኒቨርሲቲው ራስ-ገዝ ለመሆን

ከሚያደርገው ጥረት ጋር እጅግ ተመጋጋቢ እና አቅምን የሚያሳድጉ ፕሮጀክቶች ናቸው በመገንበት ላይ የሚገኙት፡፡

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ
በመጨረሻም የሚያስተላልፉት መልዕክት ካለ፡፡

አቶ አለሙ፡-
በመጨረሻ ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ይህ ፕሮጀክት እውን እንዲሆን ሀሳብ ከማመንጨት ጀምሮ መሬት ላይ እንዲወርድ ለማድረግ የዩኒቨርሲቲው ማኔጅመንት ብርቱ ጥረት አድርጓል፤ ይህ ስራ ለዩኒቨርሲቲያችን እንደ ትልቅ እድል የሚቆጠር ነው፡፡ በአሁኑ ወቅትም መንግስት አዳዲስ የግንባታ ፕሮጀክቶችን እንድንገነባ የፈቀደው ለእኛ ዩኒቨርሲቲ ብቻ ነው፡፡ ይህም የሆነው በተቋሙ አመራር ያላሰለሰ ጥረት ነው፡፡ ስለዚህ የተቋሙ ሰራተኞች ይህንን ተረድተው ለፕሮጀክቱ እውን መሆን የበኩላቸውን እንዲወጡ አደራ ማለት እፈልጋለሁ፡፡



G+8 ሕንጻ ግንባታ ስምምነት ሥነ-ሥርዓት

ህ/ዓ/ግ/ሥ/አ
ጊዜዎትን ሰውተው ይህንን ቃለ-መጠይቅ ስለሰጡን እናመሰግናለን፡፡

አቶ አለሙ፡-
እኔም አመሰግናለሁ፡፡



G+7 ሕንጻ ግንባታ ስምምነት ሥነ-ሥርዓት



G+8 ሕንጻ



G+7 ሕንጻ

**Ethiopian Civil Service University**
**Committed to Excellence in the Public Sector**

**Contact Address:**
**Hot line: +251-116-46-30-15**
**Tel.0116 46 2887**
**Fax: 0116463016**
**P.O.Box5648**
**E-mail: IPRD@ecsu.edu.et**
**Pr.ecsu@gmail.com**
**Website: www.ecsu.edu.et**
**Tweeter: @ECSU tweets**
**FM Radio:-100.5MHz**
**Facebook: Ethiopian Civil Service University**